# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>**ዜና ዘገባ**</u>

***መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም.***

***ወያኔ በሻዕቢያ ወታደራዊ ከምፖች ላይ ጥቃት ማድረሱን አምኖ መግለጫ ሰጠ፤***

***በጋምቤላ ዘግናኝ እና አሰቃቂ ግድያ ተፈጸመ፤፤***

***የቻይና የሲሚንቶ ፋብሪካ ፈንድቶ ከ 20 ሰዎች በላይ ሞቱ፤***

***ሼሁ አሁንም የሀገሪቱን ሀብት እያፈሰ ነው፤***

EthioLion.Com

በሻእቢያና በወያኔ መሀከል የነበረው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረስ ሰሞኑን በአፋር ክልል አዋሳኝ በሆኑ ቦታዎች በወያኔ የአየርና የእግረኛ ከባድ መሳሪያ ጥቃት መጀመሩ ታወቀ::

በተደጋጋሚ ግዜ ወያኔና ሻእቢያ ስድብና ዘቻ ሲለዋወጡ የነበረ ሲሆን ሰሞኑን ስድቡና ዛቻው ተቀይሮ ወደ ጥቃት መሰንዘር ተሸጋግሩዋል::

በሻዕቢያ የሚረዱ አማፅያን በቅርቡም በአፋር ክልል ውስጥ 27 የውጭ ሀገር ቱሪስቶችና ኢትዮጵያውያንን ማገታቸውንና ከእነዚህም ውስጥ 5 የሚሆኑትን መገደላቸውን ተከትሎ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚወስድ

በተናገረ በ15 ቀናት ውስጥ ወደ ኤርትራ ግዛት ዘልቆ 3 የጦር ማሰልጠኛ ካምፖችን ደምስሶ መመለሱን አምኖ መግለጫ መሰጠቱ ታወቀ::

ሐሙስ መጋቢት 6 ቀን 2004 ዓ.ም የወያኔው ቃል አቀባይ ሽመልስ ከማል የተባለው ግለሰብ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ሐሙስ በማለዳ የወያኔ ጦር ወደ ኤርትራ18 ኪሎ ሜትር ዘልቆ ገብቶ ራሚድ፤ገለሀዲን እና ጊምቢ ተብለው በሚጠሩ 3 ዋና ዋና የማሰልጠኛ የጦር ሰፈሮች ላይ ጥቃት ሰንዝሮ መመለሱን አምኖ ይፋ አድርጓል:: በጦር ሰፈሩ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠኑ ባይነገርም ከሰው ህይወት እስከ ንብረት መውደም የሚሆን ጉዳት እንደደረሰ ይገመታል::

የሻዕቢያ ቡድን አሸባሪዎችን መልምሎና በተለያዩ ማሰልጠኛዎች ውስጥ አሰልጥኖ ወደ ሀገሪቱ እያስገባ ነው በማለት ወያኔ ብዙ ግዜ ሲከስስ እና ሲወነጅል ቢቆይም እስከዛሬ ወታደራዊ እርምጃ ሳይወስድ አሁን መጀመሩ የውስጥ ችግሩን ለማርገብ ሊአስቦ የወሰደው ነው የሚል ትንታኔ በፖለቲካ ታዛቢዎቸ እየተነዘረ ይገኛል::

በሌላ ዜና በጋምቤላ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂ ኃይሎች በሰነዘሩት ድንገተኛ ጥቃት ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች የሞት እና የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ከጋምቤላ የደረሰን ዘገባ ገለጸ::

ሰኞ መጋቢት 3 ቀን 2004 ዓ.ም ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች በህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ተሳፍረው ከጎደሬ ከተማ ወደ ጋምቤላ ሲጉዋዙ የነበሩትን ዜጎች ከመኪና አስወርደው ግድያ መፈጸማቸውን ከጋምቤላ የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ከጋምቤላ 120 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ጎደሬ ከተማ ተነስተው በመጉዋዝ በነበሩት ዜጎች ላይ ጋምቤላ ከተማ ለመድረስ 20 ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው ጅቡዬ በተባለች ቦታ ላይ ከየት መጡ ሳይባል መኪናውን አስቁመው ወንዶቹን ብቻ እያስወረዱ ያለምንም ጥያቄ የገደሉዋቸው ሲሆን ሴቶቹን ደግሞ ወደ ጫካ እያዳፉ እንደወሰዱዋቸውም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

40 ሰዎችን አሳፍሮ ሲጉዋዝ የነበረው የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ውስጥ 29 ወንዶች እና 11 ሴቶች እንደነበሩ የጥቃቱ ሰለባዎች ጠቁመው በተለይ ከሹፌሩ ጀምሮ ያለ አንዳች ጥያቄ ወንዶቹን በእሩምታ ተኩስ ሲከፍቱባቸው 21 ወዲያው ሲሞቱ 8ቱ ደግሞ ክፉኛ መቁሰላቸውንና 8ቱን ሴቶች ደግሞ ወደ ጫካ አስገብተው እንደደፈሩዋቸው የጠቆመው ይሄው የደረሰን ዘገባ 3ቱ ዜጎች በመኪናው ወንበር ውስጥ ተደብቀው በማምለጣቸው ምንም አደጋ ሳይደርስባቸው ሊተርፉ እንደቻሉም ይሄው ዘገባ አብራርቶዋል::

EthioLion.Com

ጥቃት ደርሶባቸው ክፉኛ ከቆሰሉት መሀከል ሶስቱ በማግስቱ ማክሰኞ መጋቢት 4 ቀን 2004 ዓ.ም ህክምና በሚደረግላቸው ጋምቤላ ከተማ የህክምና ተቋዋም ውስጥ ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን ሌሎቹም በከፋ ስቃይ ላይ እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አረጋግጦዋል::

የወያኔ ቡድን በተለይ መለስ ዜናዊ በአኙዋኮች ላይ ጥላቻ በማሳደሩ ብቻ በተለያዩ ግዜያት አስከፊና ዘግናኝ እርምጃ እየወሰደባቸው በመሆኑ ክፉኛ በመበሳጨታቸው ወጣቶቹ እራሳቸውን በቡድን እያደራጁ በትጥቅ ትግል ለመፋለም ወደተለያዩ በረሀዎች እየገቡ ሲሆን ክልሉም በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ውጥረት ላይ እንደምትገኝ ዘገባው አብራርቶዋል::

በቅርቡ የክልሉን ባለስልጣናት በግምገማ የወጠረው መለስ ዜናዊ ከስልጣናቸው ለማባረርና በሌሎች ለመተካት ቢሞክርም ካድሬዎቹ አሻፈረኝ በማለታቸው ለግዜው አድፍጦ ዝም ያለ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ በክልሉ ውጥረት ከመፈጠሩም በላይ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ስራ ሙሉ ለሙሉ ተቋዋርጦ ያለበት ደረጃ ላይ መደረሱን ዘገባው አስረድቶ በአሁኑ ሰዓት በክልሉ የተለያዩ ቦታዎች የታጠቁ ቡድኖች በያሉበት በወያኔ ተቋዋም ላይ ጥቃት በማድረስ አደጋ እየጣሉ በመሆኑ ከመቼውም ግዜ በላይ ክልሉ በአጣብቂኝ ውስጥ እንደሚገኝ ዘገባው አስረድቶዋል::

ሰኞ እለት ጥቃት በተሰነዘረበት ወቅት ጥቃት አድራሾቹ ፊታቸው እንዳይታይ እና ማንነታቸው እንዳይለይ ጭምብል መሳይ ጨርቅ ሸፍነው እንደነበርና የሚናገሩትም ቋዋንቋዋ ለግዜው ምን እንደሆነ በውል ለይተው ያላወቁት ከግድያው የተረፉት ዜጎች ታጣቂዎቹ የያዙት መሳሪያና የታጠቁት ትጥቅ የተሙዋላ እንደነበር ገልፀው ግድያውን በፈጸሙበት ወቅት ብዛታቸው 15 እንደሚሆኑ እነዚሁ የጥቃቱ ሰለባ ተናግረዋል::

በዕለቱ ድርጊቱ ከተፈፀመ በሁዋላ የወያኔ የመከላከያ ሰራዊት እና የፌዴራል ፖሊስ በያለበት ቢበተንም ጥቃት ሰንዛሪዎቹን ማግኘት ባለማቻሉ እነ ማን እንደሆኑና ዓላማቸው ምን እንደሆነ በግልጽ አለመታወቁን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ ምናልባት የወያኔን አምባገነን ቡድን በትጥቅ ትግል የሚፋለሙ ሳይሆኑ እንዳልቀረ ሰፊ ግምት እየተሰነዘረ ይገኛል::

ከዚህ ቀደምም በዚህችው ጁብዬ በተባለችው ቦታ ላይ የህወሀት ንብረት የሆነው ሰላም ባስ የተሰኘው የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ በታጣቂዎች ጥቃት ተሰንዝሮበት የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ለሞት እንደተዳረጉ ዘገባው አስታውሶዋል::

ባለፈው ወር በጋምቤላ የግዳጅ ሰፈራ ተብሎ ዜጎች እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እየተፈናቀሉ በወታደሮች እየተደበደቡ በጭነት መኪና ተጭነው ወደ በረሀ ውስጥ ሲያጉዋጉዙዋቸው እንደነበረና ይሄንኑ በመቃወም ወደ ኬንያ የተሰደዱ ዜጎች ግማሽ ሚሊዮን መድረሳቸውን የዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ሪፖርት አጋልጦዋል::



EthioLion.Com

በሌላ ዜና ወያኔ ከሀገሪቱ ዜጎች ይልቅ ለባዕዳን ባለሀብቶች እያጎበደደ ከቀዬአቸው እያፈናቀለና እንዲሰደዱ እያደረገ የሀገሪቱንና የህዝቡን አንጡራ ሀብት እየበተነና እያደለ መሆኑ ሳያንስ ዜጎች እንደ አልባሌ በየቦታው እየወደቁ መሆኑ በይፋ ተረጋገጠ::

ደረጃውን ባልጠበቀ፤ በርካሽ እና ባልረባ ዋጋ እንዲሁም በተለያዩ ሀገራት ለዘመናት ያገለገሉ ማሽኖችን  እያስመጡ የሀገሪቱን ሀብት እያግበሰበሱ የሚገኙት የቻይና ባለሀብት ነን ባዮች በሀገሪቱ ዜጎች ላይ ከሚያደርሱት አስተዳደራዊ በደል በተጨማሪ የዜጎችን ህይወት እየቀጠፉ መሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ጥቆማ አጋልጠዋል::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ አይን ባወጣ መልኩ ከቻይና ጋር እፍ ንፍስ እያለ የሚገኘው የመለስ ዜናዊ ቡድን በፈጠረው መስመር የሳተ ግንኙነት የቻይና ባለሀብት ናቸው የተባሉ ኮልኮሌ ይዘው ለመጡት ሁሉ እያጎበደደ እና  እየተንበረከከ የሀገሪቱን ህዝብ ማንነት እስከማሰደብ የደረሰ ከመሆኑም በላይ ዜጎች በየቦታው እንደ አልባሌ እየተቀጠፉ እንዲቀሩ መደረጉም ታውቆዋል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በጎጃም መስመር ከአዲስ አበባ 150 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ገብረ ጉራቻ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው ሻንጊሽ የተሰኘው የቻይና የሲሚንቶ ፋብሪካ ፈንድቶ 15 ኢትዮጵያውያን ሲሞቱ ቁጥራቸው የበዙ ኢትዮጵያውያኖች ለከፋ አደጋ መዳረጋቸው ታውቆዋል::

የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ.ም  አሮጌ ማሽን ይዞ ስራ በጀመረው የቻይና ሲሚንቶ ፋብሪካ ውስጥ በተከሰተ የማሽን ፍንዳታ ከ30 ሰዎች በላይ አደጋ ሲደርስባቸው 20ዎቹ  ወዲያው ሲሞቱ 10ሩ ደግሞ የከፋ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው ወደ አዲስ አበባ ለህክምና በራሳቸው ወጪ መጉዋዛቸው ታውቆዋል::

ከሞቱት 20 ሰዎች መሀከል የ15ቱ አስከሬን የተገኘ ሲሆን የ5ቱ ግን የት እንደደረሰ ሳይታወቅ መቅረቱንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾ የተከሰተው ፍንዳታ እጅግ ከባድ በመሆኑ ሰውነታቸው ተበጣጥሶ ሳይበታተን አይቀርም ሲሉም በወቅቱ በቦታው የነበሩ የአይን እማኞች ገልፀዋል::

የዚሁ ድርጅት ቅርንጫፍ የሆነው በሞጆ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው ሲሚንቶ ፋብሪካ ከሶስት ወር በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ስሊንደር ፈነዳ ተብሎ 6 ኢትዮጵያውያን ሲሞቱ በርካቶች መቁሰላቸው አይዘነጋም::

በቴክኒክ እና በጉልበት ስራ በተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ላይ እያላገጡና እያሾፉ የሚገኙት እነዚሁ የዚሁ ፋብሪካ ባለቤት የሆኑት ቻይናውያን የሀገሪቱ ዜጎች የሰሩበትን የላባቸውን ዋጋ በአግባቡ ክፍያ ሳይፈጽሙ እየቀሩ ለከፋ ችግር ከመዳረጋቸውም በላይ  እንደ ባርያ አሳዳሪ ስርዓት በዱላ እየደበደቡ ሲያባርሩ በየቦታው የተቀመጡ የወያኔ ባለስልጣናት አይተው እንዳላየ...... ሰምተው እንዳልሰማ..... ከመሆናቸውም በተጨማሪ እንደ ወንጀለኛ ለእስር እየዳረጉዋቸው እንደነበርም በተደጋጋሚ አቤቱታ ሲያቀርቡ እንደነበር መዘገባችን አይዘነጋም::

በተመሳሳይ በደሀው ህዝብ ሀብት ተምረው ሀገራቸውን በቅንነት ሊያገለግሉ ደፋ ቀና ሲሉ በነበሩ ኢትዮጵያዊ መሀንዲሶች ላይ የቻይና ባለሀብት ነን ባይ እውቀት የለሾች ጥቃት ሲፈጽሙባቸው የወያኔ የህግ አስከባሪና አስፈጻሚ የተባለው አካል ምንም አይነት ጥበቃና ከለላ አለማድረጉን የጥቃቱ ሰለባ



EthioLion.Com

የሆኑ መሀንዲሶች አጋለጡ::

ያለ ጨረታ ከሻሸመኔ እስከ ባሌ ሮቤ ከተማ ድረስ የመንገድ ስራ የተሰጠው የቻይና ድርጅት ባለቤት የሰራው የመንገድ ስራ ትክክል እና ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑ እንዲያፈርስና በድጋሚ እንዲሰራ ኢትዮጵያውያ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተበሳጨው ይሄው ቻይናዊ መሐንዲሱን ደብድቦ ጉዳት ያደረሰበት መሆኑን ከሮቤ የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

በተደጋጋሚ ግዜ መንገዱ ጥራት እንደሌለው እና ደረጃውን የጠበቀ ስራ እንዳልተሰራ ለሚመለከታቸው የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሪፖርት ሲያደርግ የቆየው ይሄው ኢትዮጵያዊ መሀንዲስ ሰሚ አጥቶ ባለበት ወቅት ቻይናዊው ጠቀም ያለ ገንዘብ ሰጥቶት ማጋለጡን እንዲያቆም ቢለምነውም «የወገኔ ሀብት ሲዘረፍ መመልከት አዕይምሮዬ አይፈቅድም »በማለቱ ቻይናውያን በቡድን ተሰብስበው መሐንዲሱን ደብድበው ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሱበት ይሔው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

ኢትዮጵያዊው መሐንዲስ በቻይና ዜጎች ድብደባ ከተፈጸመበት በሁዋላ በአፋጣኝ ህክምና እንዳያገኝና ደሙ አልቆ ፈስሶ እንዲሞት ተልዕኮ የተሰጣቸው የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ የሻለቃ አዘዥ የሆነ ግለሰብ ጥፋተኛው አንተ ነህ በማለት ለረዥም ሰዓት አግቶት የነበረ ቢሆንም በወቅቱ ድርጊቱ ሲፈጸም የነበሩ ኢትዮጵያዊ ሰራተኞች በብስጭት ከፖሊሱ ጋር ግጭት ፈጥረው ካስለቀቁት በሁዋላ ወደ ሮቤ ከተማ የህክምና ማዕከል ወስደው ህይወቱ ሊተርፍ እንደቻለ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

መሐንዲሱ ላይ ጥቃት የሰነዘሩት ቻይናውያን ሳይከሰሱና ሳይጠየቁ ያለ አንዳች ችግር ስራቸውን ሲሰሩ ከመቆየታቸውም በተጨማሪ ይፍረስ የተባለው መንገድ ሳይፈርስ በነበረበት ሁኔታ ቀጥሎ በወያኔ ባለስልጣናት ተቀባይነት አግኝቶ ስራው ተጠናቀቆ ተመረቀ ተብሎ በቲሌቪዥን መነገሩ እጅግ አስገራሚና በሀገር እና በህዝብ ሀብት መቀለድ ነው ሲሉ የሮቤ ከተማ ነዋሪዎች በቁጭት ሲናገሩ እንደነበርም ተገልጾዋል::

በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ ከ300 ሺህ በላይ ቻይናውያን ዜጎች በተለያዩ የስራ መስክ ተሰማርተው የሚኖሩ ሲሆን በተለይ ከሱቅ በደረቴ ጀምሮ እስከ ቀን ስራ.....ከኢንቨስትመንት እስከ ተራ ንግድ ድረስ ተሰማርተው እየተንቀሳቀሱ ከመሆኑም በላይ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር እየተሞዳሞዱ በከፍተኛ ሁኔታ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት እየዘረፉ እንደሚገኙም ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ለ21 ዓመታት በስልጣን ላይ የቆየው የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ልጆቻቸውን ከነሞግዚቶቻቸው ወደ ቻይና እየላኩ ኑሮዋቸውን በዚያው መስርተው በኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት እየተጫወቱበት ከመሆኑም በተጨማሪ በቤንጂንግ ከተማ እጅግ ዘመናዊ ቪላ ቤት እየገነቡ እንደሚገኙም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት ቢሊየነር ሆኖ ከዓለም ቱጃሮች ጋር እየተፎካከረ የሚገኘው የወያኔ አፍቃሪ ሼህ ሙሀመድ አላሙዲን በጥቂት ቀናት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ ካዝናው ሊያስገባ መሆኑ ተጋለጠ::



EthioLion.Com

ሳዑዲ ስታር የተሰኘው የሼህ ሙሐመድ አላሙዲን የእርሻ ኩባንያ በቅርቡ በጋምቤላ ደን ጨፍጭፎ ባመረተው ከ1 ሚሊዮን ቶን በላይ ሩዝ ወደ ውጭ ልኮ ከ1ቢሊዮን ዶላር በላይ ሊያፍስ መሆኑ ተጋልጦዋል::

የሰራተኛ ደመወዝ በአግባቡ መክፈል ያልቻለው ይሄው የወያኔ አፍቃሪ ግለሰብ ዜጎች ላባቸውን አንጠፍጥፈው ሌት በቁር .....ቀን በሀሩር..... እየተጠበሱ ሰርተው ክፍያ ተነፍጎዋቸው በርሀብ እየተሰቃዩ ባለበት በዚህ ግዜ እነሱ ያመረቱትን ሩዝ ወደ ውጭ ልኮ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ሊያፍስ መሆኑ ታውቆዋል::

አፈር ግጠው ሌት ተቀን ሳይሉ የሚያመርቱትን ሰራተኞች በመናቁ የለፉበትንና ላባቸውን ያፈሰሱበትን የድካማቸውን ዋጋ ሳይከፍል በአንጻሩ ከኢትዮጵያ ምድር የታፈሰውን ሩዝ ለውጭ ገበያ አቅርቦ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ሊዝቅ ከመሆኑም በላይ በሰራተኛው ላይ እያላገጠና እያሾፈ በመሆኑ ሰራተኛው አመጽ ሊያነሳ በዝግጅት ላይ መሆኑም ታውቆዋል::

በቅርቡ ባስገባቸው ዘመናዊ ቮልቮ የጭነት መኪኖች ሰሞኑን ከእርሻው ቦታ ወደ ጋምቤላ አውሮፕላን ማረፊያ ሩዙን እያጉዋጉዋዘ ወደ አረብ ሀገራት ሊሸጥ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ ቢሆንም ሰራተኛ ው የሰራበትና የደከመበት የሁለት ወር ደመወዙ ሳይሰጠው በመቅረቱ ተቃውሞ እያሰማ በመሆኑ የፌዴራል ፖሊስ ሽፋን እንዲሰጠው መጠየቁንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

የሀገሪቱን የወርቅ ማዕድን በነጻ ለ10 ዓመታት ሲዝቅ የኖረው ይሄው ቢሊየነር ወደ ኢትዮጵያ ከመጣና ስራ ከጀመረ ጀምሮ እጅግ አስደንገጭ የሆነ እድገት ከማግኘቱም በላይ በሀብት ላይ ሀብት እንዲያከማች የወያኔ አጎብዳጅ ባለስልጣናት ስላመቻቹለት አሁን ላለበት ደረጃ ሊደርስ እንደቻለ የሚገልጹት ለሀገር ተቆርቋሪ ዜጎች ሰሞኑን በአንድ ድርጅት በተደረገ ውድድር ከአፍሪካ በገንዘብ መጠን ቀደምት ሊሆን የቻለ መሆኑ እየተነገረ ሲገኝ ለዚህ ሁሉ የበቃው የሀገሪቱን የወርቅ ሀብት እያፈሰ በመውሰዱ ነው ሲሉም ይናገራሉ::

በቅርቡ የለገደንቢ የወርቅ ማዕድን መሬት አራግፎ አጥቦ በመጨረሱ እንደገና ሌላ 50 ሺህ ሄክታር የወርቅ ማዕድን ያለበት መሬት የተሰጠው ሲሆን በጋምቤላም በተመሳሳይ 50 ሺህ ሄክታር የወርቅ ማዕድን ያለበት መሬት እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሎዋል::



EthioLion.Com